


## The Lord is Good and His Mercies endures forever

## እግዚአብሔር መልካም ነው ምህረቱም ለዘላለም ይጸናል

ውድ ጓደኞች፥

ውድ በሆነው በ**ጌታ**ችን በ**የሹዋ** ቡሩክ ስም ሰላም እላችኋለሁ፥ ውዱ **ጌታ**ችን **የሹዋ**ም ሁሉም እንዲያዩት በጣም በቅርቡ ይመጣል።

2012 ዓ.ም በቶሎ ወደ መረሳት ይሄዳል። 2012 በትንሽ ወይም በትልቅ መጠኖች ሁሉም የተጋፈጧቸው ብዙ ተግዳሮቶችና ችግሮች አምጥቶአል። አንዴ በድጋሜ እስራኤል ወደ አንድ ትልቅ ደረጃ ጦርነት በጣም ቀርባ መጥታለች። የቅዱሳኑ ጸሎት እና የ**ጌታ አምላካችን** የበለፀገ መልካምነት ብዙ የጺጋ ሰዓት ቀጥሎልናል(አራዝሞልናል)።

በዙሪያችን ምን እየሆነ ነው ያለው? ያለማቋረጥ እየተከሰተ ባለ እንዲህ ባለ ትልቅ ግርግር(ረብሻ) ውስጥ ለምን ሆንን? ጥያቄ ታነሱና ትሳቀቁ ይሆናል።

*ትንቢተ ሐጌ 2:6-7*
*6፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። ገና አንድ ጊዜ በቅርብ ዘመን እኔ ሰማያትንና ምድርን ባሕርንና የብስንም አናውጣለሁ፤*

*7፤ አሕዛብን ሁሉ አናውጣለሁ፥ በአሕዛብ ሁሉ የተመረጠውም ዕቃ ይመጣል፤ ይህንም ቤት በክብር እሞላዋለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።*

የሚከተሉት ሁኔታዎች በ**ጌታ እግዚአብሔር** እንደተደነገጉት እየሆኑ እንደሆነ ከዚህ ቃል።

1. እግዚአብሔር ሰማይን፣ ምድርን፣ ባሕርን፣ እና የብስን እያናወጠ ነው – የተፈጥሮ አደጋዎች።
2. እግዚአብሔር አሕዛብን ሁሉ እያናወጠ ነው – ትልቅ ግርግር(ረብሻ) በአሕዛብ።
3. በአሕዛብ ሁሉ የተመረጠው – **ጌታ የሹዋ**(**ኢየሱስ**) በቅርቡ ሊመጣ ነው። The Desire of All Nations – The **Lord Yeshua** is going to come soon.

በምድር ላይ በቅርቡ ለሚመጣው የ**እግዚአብሔር** መንግሥት ሰማያትና ምድር እየተዘጋጁ ነው። በ**እግዚአብሔር** ቤት ውስጥም ደግሞ የሚሆነው መናወጡ ወይም መንፃቱ (የተያያዘውን ልዩ የጽሑፍ መልእክት እባካችሁ ተመልከቱ) በቅርቡ ለሚፈስሰው የኋለኛው ዝናብ ክብር አስፈላጊ ነው (ሐጌ 2:9)። በሚመጡት ወራት እነዚህን ሁሉ በዝርዝር አቀርባለሁ(አብራራለሁ)።

በ2012 ዓ.ም ሁሉ ለእኛ – ለጸናንት አገልግሎት **ጌታ** መልካም ሆኖልናል። ከ**እግዚአብሔር** ጋር ባለኝ ባለፉት 32 ዓመታት የአገልግሎት ጉዞዬ ታይቶ የማይታወቅ በአገልግሎታችን እስካሁን ሆኖ የማያውቅ በጣም ትልቁን ተግዳሮት ተጋፍጠናል። ሆኖም፥ የእርሱ(የእግዚአብሔር) በትርና ምርኩዝ በደህንነት አሳልፈውናል። በዚህ ዓመት በኤንጅል ቲቪ አገልግሎቶች (Angel TV ministries) ከዋና ዝላይ(ፈጣን እንቅስቃሴ) እጅግ በላይ አድርገናል። ሰሜን አሜሪካ ውስጥ እና

አውስትራሊያ/ኒውዚላንድ ውስጥ ከገና 2012 ጀምሮ በሳተላይት ላይ በቀጥታ ስርጭት እናስተላልፋለን። ኑ፥ **እግዚአብሔር**ን ከእኛ ጋር አወድሱ። የመመልከቻ ዝርዝሮች በቅርቡ ይላካሉ።

ብዙ ስለታማ ትንቢትና ከፍጻሜ ዘመን ጋር የተገናኙ መርሐ ግብሮችን (ፕሮግራሞችን) ለማዘጋጀት እየፈለግን ነው። ብዙ አዲስ የትንቢት/የፍጻሜ ዘመን አስተማሪዎች በኤንጅል ቲቪ ላይ ይታያሉ። ለዚያ ጸሎቶቻችሁን እፈልጋለሁ።

የሚያስደንቁ ነገሮች በ2013 ይጠብቁናል። በትልቅ ጨለማ መካከል፥ የ**እግዚአብሔር** ክብር በብዛት ይገለጣል ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ኢሳይያስ 60:2)። የምትጸልዩና የምትተጉ ሁኑ። Be praying and watching.

በ2012 ሁሉ ስለጸለያችሁልንና ስለረዳችሁን እናመሰግናለን። ለ**እግዚአብሔር** የበለጡ ታላላቅ ሥራዎችን ለማድረግ ስንንቀሳቀስ መጸለያችሁንና መርዳታችሁን እባካችሁን በ2013 ቀጥሉ። **እግዚአብሔር** እንድናደርገው ስለጠየቀን ስለሁሉም አዳዲስ ነገሮች በቅርቡ ከእኛ ትሰማላችሁ።

የተባረከ የገና አከባበር ይኑራችሁ። Have a blessed Christmas celebration.

ከፍቅር እና በረከቶች ጋር

ሳድሁ ሱንዳር ሴልቫራጅ

http://www.angeltv.org , http://fireofgodservants.blogspot.com/ , http://www.thelordshour.com , http://www.choothomas.org , http://www.Jesusministries.org/, http://www.Billygraham.org , http://free.messianicbible.com/ , http://www.levitt.tv/ , http://www.baptizingfire.com

http://www.divinerevelations.info/amharic , http://www.heavenvisit.com , http://www.tribulation-now.org , http://www.voe.org/ , http://www.sidroth.org , http://repentandpreparetheway.org/ , http://www.theblazingholyfire.com/ , http://www.shekinahworship.com/ , http://www.thelastreformation.com , http://www.be4thefire.com/ , http://www.e-sword.net/

http://www.annarountree.com/ , http://www.beyondthephysicalrealm.com , http://www.shreveministries.org , http://www.blogtalkradio/tribulation-now , http://www.blogtalkradio/thelordshour , http://www.blogtalkradio.com/discoveringthetruth , http://www.bullsere.kr/